የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ ብራስልስ
Embassy of The Federal Democratic
Republic of Ethiopia - Brussels

ቀን፡
Date፡ ጥቅምት 17 ቀን 2019 ዓ.ም.

# ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

## የሕጻናት አዲስ ፓስፖርት እና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እድሳት አገልግሎት ተጀመረ

### በቤልጅየም፣ ኔዘርላንድስና ሉግዘምበርግ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

- ✓ በ E-Pass መተግበሪያ አማካይነት በኦንላይን ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል የህጻናት አዲስ ፓስፖርት እና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እድሳት አገልግሎት የተጀመረ መሆኑን እየገለጽን አመልካቾች፡-
  - አገልግሎቶቹን ለማግኘት immigration.gov.et የሚለዉን ዌብሳይት አድራሻ በመጠቀም፣
  - አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት፣
  - በመተግበሪያዉ ላይ ያለዉን የቀጠሮ መስጫ ፎርም በመጠቀም ወደ ኤምባሲ በመምጣት አሻራ የሚሰጡበትን የቀጠሮ ቀን በመሙላት እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያዉን በካርድዎ አማካይነት በመፈጸም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ሲሆን፡-
- ✓ አገልግሎቶችን ለማግኘት መሟላት የሚኖርባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች በተመለከተ፡-

1. ለህጻናት አዲስ ፓስፖርት ፣
   - የህጻኑ የልደት ሰርትፍኬት፣ (በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ፣ የአባት እና የእናት ስም በተሟላ ሁኔታ የተካተተበት)
   - የአባት እና የእናት የኢትዮጰያ ፓስፖርት፣ (የአገልግሎት ጊዜ ያለዉ)
   - የአባት እና የእናት የመኖሪያ ፈቃድ ፣ (የአገልግሎት ጊዜ ያለዉ)
   - የአባት እና የእናት ID ፣ (የአገልግሎት ጊዜ ያለዉ)
   - ከወላጆቹ አንዱ የሌላ አገር ዜግነት ያላቸዉ ከሆነ ህጻኑ የሌላ አገር ዜግነት የሌለዉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣
   - ህጻኑ በቅርብ ጊዜ የተነሳዉ የፓስፖርት ፎቶ፣

2. የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) እድሳት አገልግሎት፡-

   2.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ለህጻናት፡-
   - የህጻኑ ዜግነት የያዘበት አገር ፓስፖርት ( ከ6 ወር ጊዜ በላይ ያለዉ)
   - የልደት ሰርትፍኬት፣ ( በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ)
   - የወላጅ የኢትዮጵያ መታወቂያ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ( ከ6 ወር ጊዜ በላይ ያለዉ)
   - ጊዜዉ ያለፈበት የህጻኑ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ፣
   - ✓ አመልካች አሳዳጊ ወይም ጉዲፈቻ አድራጊ ከሆነ ፡-
   - የአሳዳጊዉ ወይም ጉዲፈቻ አድራጊዉ ፓስፖርት ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ፣
   - አሳዳጊ ወይም ጉዲፈቻ አድራጊ መሆኑን የሚያሳይ የፍርድ ቤት ዉሳኔ፣ ( በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብራስልስ Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia

**2.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ለአዋቂ፡-**

- ዜግነት የያዘበት አገር ፓስፖርት (ከ6 ወር ጊዜ በላይ ያለዉ)
- ጊዜዉ ያለፈበት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ፣

**2.2 አመልካች እርማት (Correction) ከሆነ የሚያመለክተዉ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፡-**

- **የስም ለዉጥ ከሆነ፡-** የፍርድ ቤት ዉሳኔ፣ (በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ)
- **የትዉልድ ቀን ማስተካከያ ከሆነ፡-** የልደት ሰርትፍኬት፣ (በዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ)
- **ዜግነት ማስተካከያ ከሆነ፡-** ዜግነት የያዙበት አገር ፓስፖርት ( ከ6 ወር ጊዜ በላይ ያለዉ)

**2.3 አመልካች የጠፋ (Lost) ከሆነ የሚያመለክተዉ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፡-**

- የፖሊስ ማስረጃ

**2.4 አመልካች የተበላሸ (Damage) ከሆነ የሚያመለክተዉ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፡-**

- የተበላሸዉን የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ማቅረብ የሚያስፈልግ መሆኑን በአክብሮት ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

**የኢትዮጵያ ኤምባሲ ብራስልስ**

**አክቶበር 27 ቀን 2026 ዓ.ም.**